# <u>ለደብተራው ቀን  እና ለደብተራው ድረ-ገጽ ሁለተኛ አመት በአል መልእክት</u>

የደብተራው ድረ-ገጽ ዝግጅት ቦርድ እና የደጋፊዎቹ ክበብ አባላት፡-

በቅድሚያ የዚህን ዝግጅት የክብር እንግዶችና መላ ታዳሚዎች እንኳን ደህና መጣችሁ እንላለን። በትብብርም ይህን ቀንና የድረ-ገጻችንን ሁለተኛ አመት ለማክበር ዝግጅቱን በማቀናበር ለተባበሩት አሲምባ የውይይት መድረክ እና ለፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ ጣቢያ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

ደብተራው ድረ-ገጽ ስሙን የያዘው ከጸገየ ወይን (ከጸጋዬ) ገብረ-መድህን ወይም ከደብተራው መሆኑ ግልጽ ነው ። ይህን ቆራጥ ታጋይ እና የተዋጣለት ገጣሚ ለማስታወስ። በእሱ ተምሳሌነትም ግላዊ ህይወታቸውን ለሀገርና ለህዝብ ቤዛነት አሳልፈው ለሰጡ ሁሉ ቆሟል።

የዛሬ ሁለት ሁለት አመት ድረ-ገጹን የጀመርነውም በነኝህ ብርቅ የኢትዮጵያ ልጆች አኩሪ ገድል ላይ ከለየለት ጠላት በተጨማሪ መሰሪዎች፣ እነጊዜ ሰጠንና ጥራዝ ነጠቆች ሊለጥፉ የሚሞክሩት ጭቃ አስቆጭቶን ነው፣ የሀገራችን የብዙዎቹ ፖለቲካ ተዋንያን ሌላው ቀርቶ የሰብአዊ መብት ተከራካከሪ ነን የሚሉት እንኳ ጸጋዬንና ጓዶቹን ለማንሳት አለመፈለጋቸው እልህ አጭሮብን ነው። ድረ-ገጹም ለጊዜው ያየለው የጸረ-ህዝብ ጎራ በነኝህ የህዝብ ልጆች ላይ ሊያጥል የሚከጅለውን ጨለማም እየተዋጋ ሊዘክራቸው ይሞክራል። እነኝህ የህዝብ ልጆች የቆሙላቸውን መሰረታዊ መርሆዎች ማለትም

1. የኢትዮጵያን አንድነት፣
2. የህዝቧንም የዴሞክራሲ መብት ትግልና ህልውና ለማሰናከል እስካልታለሙ
3. በአቀራረባቸውም ዝግጅት ቦርዱ የነደፈውን ደረጃና መስፈርት የጠበቁ እስከሆኑ ድረስ

የጽሁፍ፣ የድምጽና የቪድዮ ስራዎችን ያስተናግዳል። በሀገራችን የተተከለውን ጸረ-ህዝብና ጸረ-ኢትዮጵያ አገዛዝ የመታገል ኢላማ ሳይስትም ሀሳቦች በነጻነት እየተንሸራሸሩ፣ የድረ-ገጹ ጎብኝዎች ጠቃሚ መረጃ፣ ፍሬ ያለው ግንዛቤ እንዲጨብጡ ጥረት ይደረጋል።

ቀደም ሲል የተጠቀሱት ዋና የዝግጅት መርሆዎች የሚያፋልስ እስካልሆነ ድረስም ሚዛናዊ እና ሁሉን አቀፍ መሆን እንዳለብን እናምናለን። ለመሆንም ሞክረናል፤ ዱሮም ከምንጠብቃቸው ወገኖች በኩል ይሰነዘር የነበረውን የጥላቻ፣ የጥቃትና ኢላማ የማሳቻ መልእክት ቸል እያልን። ከጊዜ ጊዜ ጽናትንና ግንዛቤን እያዳበረልን የመጣው የቋሚ አምደኞቻችን፣ የአበረታቾቻችን፣ የጎብኝዎቻችን ድጋፍና እገዛም ዋና ሃይላችን ነው። ለወደፊቱም ይህ እንደሚቀጥል ሙሉ ተስፋ አለን።

ሁለተኛ አመታችንን ስናከብር የትግል ቃል ኪዳናቸውን ጠብቀው ሲፋለሙ ከወያኔ እጅ  ወድቀው ላለፉት17 አመታት ያሉበት የማይታወቀውን ጸጋየ ገብረመድህን (ደብተራውን) እና ሌሎቹንም ጓዶቹን በልቦናችን እያሰብን ነው። ድረ-ገጹም የያዘውን ስም ከቆመለት አላማ ጋር አቆራኝቶ የሚጠበቅበትን ሆኖ እንደሚገኝ ቃል እየገባን ። እዚህ ላይ ደብተራው ድረ-ገጽ ከማንም ድርጅት ጋር ያልተያያዘ እና  ከዝግጅት ቦርዱ ውጭም ከማንም አካል መመሪያ የማይቀበል መሆኑን እናስታውሳለን። ነገር ግን ከኢትዮጵያ ህዝብና ኢትዮጵያዊነት መወገን፣ ለሰብአዊ መብቶች መከበር መሟገት፣ በትግሉ መስክ ለክቡር ዓላማ በክብር የወደቁ ወይም መከራ በመቀበል ላይ ያሉ ጀግኖችን ማክበር፣ እነኝህ ጀግኖች ከበፊቱም ህሊናቸውን በወሰዱት አቋም ነፃ አውጥተዋልና ለአካላዊ ነፃነታቸው መፋለም፣ ለዴሞክራሲ እውን መሆን የሚታገሉ ሃይላትን ማገዝ፣ አምባገነንነትን መታገል እንዳለብን ምንም ብዥታ የለንም። ስለዚህምድረ-ገጹ ከኢትዮጵያ እና ከኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ጎን ሚና የለየ ነው። ይህም ይቀጥላል። የትም ይሁን የት የህዝብ መገናኛዎች ገለልተኛ መሆን አለባቸው ሲባል በተዛማጅ (relatively) እንጅ የሀገርና የህዝብ ህልውናን አሳልፎ እስከሚሰጥ ድረስ እዳልሆነ ልብ ልንል የሚገባ ይመስለናል። ለዚህም ነው በኢትዮጵያ እና በህዝቧ ህልውናና አንድነት ላይ ወለም ዘለም አንልም የምንለው።

በመጨረሻም ከሚያረካ የስራ ውጤት ጋር ሁለተኛ አመቱን ለማክበር ይችል ዘንድ በተለያየ መንገድ አስተዋጽኦ ላደረጋችሁልን ቋሚ የደብተራው አምደኞች፣ ደጋፊዎች፣ ጎብኝዎች፣ ድረገጾችንና ሬዲዮ ጣቢያዎች ጨምሮ በተለያዩ የህዝብ መገናዎች ለምትሰሩ ተባባሪ የሙያ አጋሮቻችን፣ ይህን ቀን በትብብር ላዘጋጃችሁልን ለአሲ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ምባ የውይይት መድረክ እና ለፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ ሬዲዮ ጣቢያ ምስጋናችንን እናቀርባለን። በድጋ
ሚም የዚህን ዝግጅት የክብር እንግዶችንና ጠቅላላውን ታዳሚዎች እንኳን ደህና መጣችሁ! እንኳን ለድረ-ገፃ
ችን ሁለተኛ ዓመት አብሮ አደረሰን እንላለን!

ጸጋዬ ደብተራውና ሌሎችም በወያኔ እስር ቤት የሚማቅቁ ታጋይ የህዝብ ልጆች ሁሉ ይፈቱ!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!
የኢትዮጵያ ህዝብ ያቸንፋል!

የደብተራው ድረ-ገጽ ዝግጅት ቦርድ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com